# <u>እንጻፍ ካልንማ (4)</u>

*"ስፈልግ ነኝ የሚል ኮርቶ የሚያኮራ*

*ልቤን አቆሰለው የነበርን ጫጫታ" ።*

*ከ ኢያሱ ዓለማየሁ*

ታሪክ ቅርስ ነው። ያለፈውን በምጸት ወይም በመኩራራት ለማስታወስ ብቻ ሳይሆን ለብሩህና የተሻለ ነገን እውን ለማድረግ ለሚደረገው ትግል መሳሪያ ነው ። አልያማ ትኩሱ ሬሳ ደረቁን አስረሳ ዓይነት ይሆንና አጼን ሙገሳ፤ ውድቁን ፋሺስት መናፈቅና ሊወገር የሚገባው ዘረኛና ነፍሰ ገዳይ ሲሞት ደረት ድለቃ ሊከተል ይችላል ። ከወያኔ ጋር ተጣምሮ የመጣና የህዝብን ትግል የጎዳው አንዱ ክስተት ወይም ጽንሰ ሀሳብ ስልጡን ፖለቲካ የሚባለው ነው ። ይህ አምርሮ መታገልን የሚተች አቅዋም በለሆሳስና በጩኸትም ሊያሰፍን የጣረው ፍርሃትን፤ ለጠላት መልፈስፍን፤ በባዕድ መተማመንን፤ እጅ መስጠትንና በአጠቃላይ ቀቢጸ ተስፋን ብልጠት ብልህነት አስመስሎ ማቅረቡ ነው ። ወያኔ ስልጡን ፖለቲካን አፍቅሮ ቢገኝ የሚያስገርም አይደለም ። ትግል አልበገር ያለውን የገዢዎች ምሽግ እናፈርሳለን የሚል መንፈስን ያቀፈና ሁሉም ጭራቆች ይወገዳሉ ባይ ሊሆን ሲገባው የሚቻል ፖለቲካ--ገና ሳይነሳ ራሱን የወሰነና ያሸመደመደ-- ስልጡን ተብሎ በመቅረቡ ትግላችንን ጎድቷል ። ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር ብዙ ነጮች በጦርና ጋሻ፤ በምኒሺር ደረጃ ታጥቀው የተሰለፉት አርበኞች ላይ ሞኞች ብለው እንደተሳለቁት ሁሉ ማለት ነው ። ዛሬም ሆነ ዘገየ፤ ተፈለገም ተጠላም ግን የድል አብሳሪ ትግል ወያኔን በሀይል በአመጽ የሚያጠቃና እግረ መንገዱንም ስልጡን መሆን ሳይሆን ቆራጥነትና መስዋዕትነትን የሚጠይቅ መሆኑ አይቀሬ ነው ። ጨዋነትና ባርነትን መቻል ተወራራሽ አይደሉም ።

በአሁኑ ጊዜ በተለይም ከወያኔ ጋር የተደላደለ ኑሮና ይዞታ ያላቸው ክፍሎች ያለውን ትውልድ በመተቸትና በማውገዙ ላይ ማተኮራችው ይደመጣል ። ሰዉ ሁሉ--ድህው ከበርቴው-- የራሱን ኑሮ ለማሻሻል ነው የሚሯሯጠው፤ ለሀገር ደግ ቢመኙም ጊዜ የለውም ይሉናል ። ለራሳቸው መፋዘዝ ሕዝብን ተጠያቂ ሊያረጉ ይጥራሉ ማለት ይቻላል ። እንደ ዱሮው አይደለም ሰዉም ሁኔታውም የሚል ማሳሰቢያም ሲሰጠን ቆይቷል ። ይህን በተመለከተ ታሪክን እናንሳ ካልን የያኔው የተማሪ እንቅስቃሴ በመጀመሪያ የብዙሃን እንቅስቃሴ አልነበረም ። የተወሰኑ ጽኑ መሪዎችና ታጋዮች ናቸው እንቅስቃሴውን ሊያጠናክሩትና ተደማጭነት/ተቀባይነት ሊያሰጡት የቻሉት ። ግንባር ቀደም የነበሩት ዘጠኝ የተማሪው እንቅስቃሴ መሪዎች-- ሀይሉ ገብረዮሓንስ/ገሞራው/፤ ብርሃነ መስቀል ረዳ፤ ዘሩ ክህሸን፤ ሚካኤል አበበና ሊሎችም ከዩኒቨርስቲ ሲባረሩ እነሱ ካልተመለሱ ትምህርት አንገባም የሚል ተቃውሞ ተማሪው አላሰማም። በቀጣዩም ሰልፍ ሲደረግና ዩኒቨርስቲው ሲዘጋም ትምህምርት ለመቀጠልና ከተቃውሞው ለመራቅ የጣሩት ጥቂቶች አልነበሩም ። ያ የጥቂቶች--የቆራጦች-- እንቅስቃሴም በጊዜ ሂደት ብዙዎችን ሊያሰባስብና ሊያቅፍ ችሏል ። አንዳንዶች የያኔ ወጣቶችን የባዕድ ርዕዮት ተከታይ አድርገው በመፈረጅ ሊያወግዙ ብዙ ጥረዋል ። በአንጻሩ ግን ሊበራሊዝም ወይም ካፒታሊዝምን እናፈቅራለን ሲሉ ይህ ርዕዮት በዋልድባ እንዳልተፈለሰፈ የምናውቅ አይመስላቸውም ። ዛሬ ያ የፈረደበትን ዋለልኝ ኢትዮጵያዊነቱን ሊቀሙት፤ ሀገር ብሎ አፍቅሮና ቆርጦ የሞተላትን ሀገር ከዳ ሊሉ የሚከጅሉት ሁሉ ጥያቄው እናንተስ ያኔ የት ነበራችሁ ቢባሉ የሚያኮራ መልስ የሚሰጡ እለመሆናቸውን የምናውቀው ነው። ወደ ቁም ነገሩ ለመመለስ ግን ዛሬም ወጣቱ ትውልድ አርአያ የሚሆነውና የሚያታግለው ካለ ለሀገሩና ለወገኑ የሚታገልና የሚሰዋ መሆኑን በየጊዜው አሳይቷል ። የሚያሳዝነው ትግሉን እንመራለን

የሚሉት ብቁ  አታጋይ ሊሆኑ አለመቻላቸው ነው ። የታገለውን ትውልድ ታሪክ የሚከልሱና የሚያቆሽሹ መብዛታቸው ነው ብንል ስህተት አይሆንም ።

ትግል ስለተባለ ብዙሃኑ ሆ ብለው በሰልፍ አይገኙም ።  ብዙ ጥረትን ይጠይቃል ፤ ሰውን ማደራጀት ማሰባሰብ ፡፤ ያ ግዙፍ ሊሆን የቻለው የተማሪዎች የወጣቶች እንቅስቃሴ በመጀመሪያ ሰሞኑ የጥቂቶች እንቅስቃሴ ነበር ። ከታጋዩ ዝምተኛውና ተቃዋሚውም ይበዛ ነበር ። ዩኒቨርስቲው አስተዳደር/ለአሜሪካ ያደሩና የተደራጀውን ሊያፈርሱም አምርረው የታገሉ ነበሩ። እዚህ ላይ ነው የጽናትና የመደራጀት ጉዳይ ብቅ የሚለው። ጽናት በመኖሩም፤ የመደራጀትን ተግባር በቀላሉ ስላልተያዘ ትግሉየሚጠይቀውን ዋጋ ሊከፍሉ ዝግጁ የሆኑ ወጣቶ በመኖራቸውም እንቅስቃሴው ሊስፋፋምና ሊጠናከር ቻለ ። ዛሬም አርአያ የሚሆኑ መሪዎችና ድርጅቶች ከተገኙ ወጣቱ እናት ሀገሩን ሊታደግ ና ሊሰዋላት ዝግጁ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም ። ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባም ፤ግንጠላን ሲያጅብም፤በ1997 ምርጫምና ከዚያም በኋላ ወጣቱ ቁርጠኛነቱን አሳይቷል ። በ ጸረ ወያኔ ትግል ተካፍሏል። ሽብረክ ያለው ወጣቱ ሳይሆን የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ነን ያሉት ግለሰቦች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ድርጅት ከቶም አያስፈልግ የሚሉና በዚያው አፋቸው ደግሞ የትግሉ መሪ ሊሆኑ ሲከጅሉ የሚሰሙ እንዳሉ መዘንጋት የለብንም ። ከሕዝብ ትግል ተመክሮ መማር ያቃታቸው ብንል ትክክል ነው ።

የነበረ ሁሉ ስለነበረው የሚያወሳው ሙሉ በሙሉ ሀቅ ነው ብሎ መደምደም ባይቻልም ቢያንስ በቦታው የተገኘውንና በስማ በለው ደረጃ የሰማውን ሀቅ ብሎ የሚያቀርበውን በአንድ ማየት አይቻልም ። ኢሕአፓን በተመለከተ ሊያጠቁት ፈላጊዎች ጥቂት ስላልሆኑ ታሪኩ ብለው ሲያቀርቡ ብዙዎቹ ስለምን እንደሚጽፉ ማወቅ አይቻልም ። ከበሬ ወለደ ባሻገር የሚፈጥሩትም ትረካ ሀሰተኛ ምስክር ጉልበት ይሰብር የሚያሰኝባቸው ነው ። የኢሕአፓን የፖለቲካ መርሃ ግብር መጀመሪያ ያየው ሳዳም ሑሴን ነው ሲል አንዱ ምሁር በይፋ ከሶ ነበር--አሜሪካን ያሳስብ ካልሆነ ከሀቅ ግንኙነት የለውም። የኢሕአፓ የፖለቲካ ፕሮግራም በ1967 በ አማርኛና ሌሎች የሀገር ቋንቋዎችና በእንግሊዝኛ ወዘተ የተሰራጨው በቅድሚያ በመላ ኢትዮጵያ ነው ። የድርጅቱ መርሃ ግብር በአረቦች ተጻፈ ያለም ሀፍረተ ቢስ ነበር ። ከዋሹ አይቀር ይቀደዱ ነው ነገሩ። ተነግሮ የማያልቅ ውሸት ተዋሽቷል--ደካማና አላዋቂዋቾችንም አታሏል። ወያኔም ይጠቅመኝ ብሎ አራግቦታል፤መድረክንም ለግሷል። ማማት የለመደ አፍ ሲዶልት ያድራል ብለዋል አዛውንት ። ለገበያ የሚያመች ስለሆነም ኢሕአፓ ብለው ሶምሶማ መርገጥ ሳይሆን ላጥ ብለው ሲሮጡ ይሉኝታ የሚባል ልጓም ያዝ አያደርጋቸውም ። ምስክር የጠፋም ይመስል የማይዋሹት የለም። መሰከርን፤ ምስጢሩን አሰጣነው፤ ዕንቆቅልሹን ፈታነው፤ ሲሉና ይህንንም ወያኔና ሌሎችም በአታሚነት ሲረዷቸው አይተናል፤ እያየንም ነው ። ያቺም ጣሊያን እንደበተነው እንደረጨው የባንዳ ፈታውራሪነትና ደጃዝማች ዓይነት ዶክተር የምትል ከየጉራንጉሩ የምትገኝ ወይም የምትገዛም ታፔላ የተጻፈውን ሀቅነት የምትሰጥ ናት፤የምታስመስል ናት ተብላ መለጣጠፏም አልቀረም ። ከንቱ ልፋት፤ መማር ለመደንቆር !

" እየነገርናቸው እያረገጉት ዋዛ

ከተለበለበው የተላጠው በዛ "   እንደተባለው ሁሉ

"ስንቴ ብነግራቸው እያሉን አልሰማ

መወናበድ በዛ በዋሾዎች መንጋ"  ማለትም ተገደን አለን ።

የዋሾ አፉ ምላጭ እንበልና ይህ ሁሉ ጸረ ኢሕአፓ ዘመቻ ትኩረቱ በወጣቱ ወይም በአዲሱ ትውልድ ላይ ነው ። እኛና ታላቆቻችንማ ታግለን ኖረነዋልና የድርጅቱን ታሪክ ጠንቅቀን እናውቀዋለን ። ወጣቱን ግን 17 ዓመት ፋሺስቶቹ ሲዋሹበት ከርመው ወያኔ ደግሞ 24 ዓመት ሲቀልድብን አዲስ ጎልማሶችን የሀሰት ታሪክ እያድበለበለ ጣፋጭ ጥኸሎ ብሎ ሊያጎርስ ሲሞክር ቆይቷል ። ኢሕአፓ ወያኔን ገና ከናቅፋ ደደቢት ውልደቱ ጊዘ ጀምሮ ነቅቶበት አምርሮ የታገለው ነውና ድርጅቱን ለማጥፋት የሁሌም ምኞቱና ፍላጎቱ ነው ። በፊትም በቅርብም ፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮን ለማፈን መጣሩ ለዚህ አንድ ምስክር ነው ። ኢሕአፓን ይፈራል፤ሊፈራም ይገባዋል ። ውያኔን ሊያጠፋ እንጂ ሊያቅፍና ሊለማምመጥ የቆመ ድርጅት ባለመሆኑ ። የወያኔ የባዕድ ረዳቶች ደግሞ የኢሕአፓን ታሪክ ሳያውቁት ቀርተው አይደለም የሚቀባጥሩት ። ኢሕአፓ የባዕዳንን ጣልቃ ገብነት አውግዞ፤የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ይከበር ብሎ  ብቻ ሳይሆን በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃም ከጭቁን ሕዝቦች ጎን በመቆሙ በጠላትነት ፈርጀውታል ። አሜሪካም፤ምዕራቡም፤ ሶቪየትና ጭፍሮቹ ሁሉ ሰርገው ሊገቡት፤ሊጎዱት በየጊዜው ሲሞክሩ እንደነበር የምናውቀው ነው ። ጥረታቸው በአብዛኛው ቢከሸፍም ሰርገውን የገቡ ጥቂቶች እንደነበሩ የሚካድ አይደለም ። ሶማሊያም ወያኔም ሻዕቢያም ሊሰርጉን መሞከራቸው የጠበቅነው ነበርና ከጥቅም ውጪ ማድረጋችንን እነሱም የሚያውቁት ነው ። የባዕድ ጋዜጠኞች እነ ወያኔን ሲያሞግሱ ና ሲደግፉ ኢሕአፓን ግን ያጥላሉና ትምክህተኛ አማራ ብለው ሲያወግዙ እንደነበርም የምንረሳው አይደለም ። ዳን ኮኔል፤ጌይል ስሚዝ፤ ዴቪድ ኦቶዌይ፤ፒተር ኒግሊ ፤ፒተር ያንግ፤ አሌክስ ደ ቫል  ወዘተ ሲጽፉ የነበረውን ዝቃጭ ሁሉ ያስታውሷል ። የአምኔስቲ ኢንተርናሽናሉ ሚቼ ማርቲን ሂል ለዓመታት የገንጣዮች አፈ ቀላጤ ሆኖ ሲቆይ በወያኔ ደብዛቸው የጠፋውን የኢሕአፓ መሪዎችና አባላት ስም ሳያነሳ ህይወቱ አልፋለች ።

ታሪክን መቀማትና መበረዝ የሕዝብን ህልውናና ሀገርን ከመቀማት ዘመቻ ጋር የተቆራኘ ነው ። በርማ ብቻ አይደለችም ዛሬ ሙስሊም ሮሂንግያ የሚባል ሕዝቤ የለም--አይደለም ብላ የምትክደው ። ቱርክ አርመኖችን አልፈጀሁም ሲል ቆይቷል። ሶርያ ለኩርዶች ዜግነትን ሳይሰጥ ዘመን አልፏል ። እስራኤል የምስረታ በዓሌ የምትለው ለፍልስጤሞች የመርገም የሀዘን ቀን (አል ናቅባ ) ነው ። በኤርትራ ታሪክ ተቀምሞ ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ሆነች ። ኦነግም እስከዛሬ የቅኝ ገዢን አቅዋም እሹሩሩ እያለ ድል አልባ ሆኖ ቀርቷል ።ወያኔም መገንጠልን አቀንቅኖ አልሆን ሲለው ዘዴ ቀይሮ ብቅ አለ እንጂ ሀቀኛ የትግራይ የጭቆና ታሪክ በሚል ያላወራው ተረት አልነበረም ። አርበኞችን ቦታ ለማሳጣት ባንዳዎች--የባንዳ ጨዋ የለውምና--ለራሳቸው አዲስና ሀሰት የሆነ ታሪክ ይሰጣሉ ። ዛሬ በኢሕአፓ ይህን አድርገን ነበር ፤ይህን ሰርተን ነበርን፣ መስራች ነን፤ ወዘተ በሚል አንዳንዶች ስደት ለወሬ ያመቻል በተባለው ዓይነት የሚዋሹትን መስማት ብቻ ይበቃል ።

አሜሪካ የሚደግፈው ይህ ወጣቶችን የማደናገርና ከሀቀኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ጋር የማጣላት ዘመቻ በወሬ ብቻ ወይም በቃል ደረጃ ብቻ ታቅቦ የቆየ ሳይሆን በአፍራሽና አጥፊ እርምጃዎችም የታጀበ ነበር ። ደርግን አፍርሶ ወያኔን በቦታው ለመተካት አሜሪካ--በጎርባቾቭም እርዳታ--በኢትዮጵያ ህልውናና ሉዓላዊነት ላይ የፈጸመችው ወንጀል የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው ። ወያኔና ሻዕቢያን ብሎም ኦነግን ለመርዳት አሜሪካ ይሁነኝ ብሎ የመረጠው ጸረ ኢትዮጵያ ፖሊሲ ቀደም ብሎ የተጠነሰሰ ለመሆኑ ታሪክን የሚያውቁና በትግል አካባቢ የነበሩ ሁሉ ተችተውታል ። ኢትዮጵያ መዳከም አለባት የሚለው አቅዋም መሰረታዊ የአሜሪካ አቃዋም ነበር። አንዳንዶች የአሜሪካ ሰርጎች ገቦች እጅ አለበት ብለው በሚጠረጥሩት የኢሕ አፓ ሰራዊት ብተና  ሂደት ሳቢያ የተበተኑት ተመልሰው በድርጅቱ እንዳይሰባሰቡ ማራቅ የሚል ዕቅድ ተጠንሶና ለሱዳንም ቀርቦ ብዙዎቹን ወዲያውኑ ወደ አሜሪካ ማጓጓዝ--ማስፈር መካሄዱን እናውቃለን ። ኢሕአፓም ብተናውን ያደረሰበትን ችግርና ቀውስ ተቆጣጥሮ እንደገና ትግሉን ሲቀጥልም በጭልጋ  ቋራ  ጥቃት ሊያደርስበት በቀጥታ በሲአይ ኤ፤ ሻዕቢያና

የሱዳን የሚሊቴሪ የስለላ ተቋም የተደራጀ ና አዳዲስ የቻይና መሳሪያ የታጠቀ ሀይል ኢሕአሡን ሊያጠቃ ሞክሮ ድባቅ ተመቶ ሴራው ከሽፏል ። ግቡ የነበረው ኢሕአፓ/ሠ ን አጥፍቶ የነደረጀ ዴሬሳ ኢሕዴአ/ኢፒዲኤ ለመትከልና ሻዕቢያ በሚሰጣቸው የጦር አስረኞች ለማጠናከርና የኢፒዲኤንም ሱዳን የተተከለ ራዲዮ ወደ ሀገር ለማስገባት ነበር ። ሻዕቢያና ሲአይ ኤ የደርግን ጦር ለነሻዕቢያ በሚያመች ደረጃ ለመከፋፈል ሳይጀመር ያለቀለት መፈንቅለ መንግስት አስሞክረው እንደነበር ሲታወቅ ለዚህም ተባባሪ የሆናቸው አረመኔው ኮለኔል አንጋፋ የጦር ጄኔራሎችን ገድሎ ያደረሰው ጉዳት ታሪክ ገና ዝርዝሩ የተነገረ አይደለም ። በመፈንቅሉ ተሳትፈው ወደ አሜሪካ የሮጡ ጄኔራሎችም ዝርዝር መረጃና ዘገባ ለአሜሪካ እንጂ ለሚመለከተው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አልሰጡም ። ይህ ሁሉ ታሪክ አስተማሪና አልፎም አስጠንቃቂ ሆኖ እያለ ዛሬም አሜሪካን እንደ ወዳጅ መማጸን፤ አሜሪካ ቅጥረኛ ያደረገቻቸውን ታጋይ ብሎ በትከሻ መጫንና ሀገር ጎጂ መጃጃልን ማቀፍ ሰፍኖ ይታያል ።

ከታሪክ አንጻርም ማንን መሪ፤ማንን ጀግና ፤ማንን ታጋይ ብሎ መመዘን እንደሚገባ ያለው ውኸንብር ከታሪክ ብረዛው ጋር የተያያዘ ነው ። ባንዳ አርበኛ ፤ ገንጣይ ታጋይ፤ ቀይ ሽብርተኛ ሀገር ወዳድ ጓድ፤ አንጃ አብዮተኛ ሲባል ትውልድ ማን ቢወልድ ማ ቢጠፋውና ቢደናገር የሚያስገርም አይሆንም ። 20 ሺ አባላትን ለወያኔ አስረክቦ በመውጫ ቪዛ ፍቃድ መለስን ተሰናብተው ሀገርን የሚለቁ ማፈሪያ ሊባሉ ሲገባ መሪ ሲባሉ የተዛባ ነገር እንዳለ ግልጽ ነው ። ግለሰቦች በታሪክ ያልነበራቸውን ቦታ ሊይዙ ሲጥሩ አዲስ ታሪክ ማሰራጨታቸው የግድ ይሆንባቸዋል ። በቅርቡ፤ ያውም ያኮራ ይመስል፤ ያውም በሀሰት፤ የሻዕቢያውን መሪ እናውቀው ነበር ፤ አግኝተነው ነበር ብለው መለፈፍ የመረጡትን መታዘብ እንችላለን ። አንዳንዶች አንጃ ብለው ሌሎችን ያወገዙና ያጠቋቸውን ዛሬ መለስ ብለው ከደሙ ንጹህ ነን ዓይነት "ልክ ነበሩ እነሱ" ሲሉም አድምጠን አፍረንባቸዋል ። ዘመናዊ ጴጥሮሶች! ሕዝብን ከደን ለፋሺስት መስገዱና ለሹመት መዋረዱ የማይሆንልን ሆኖ በመታገላችን መቸም ሆነ ማንንም ይቅርታ የምንጠይቅ ባለመሆናችን ደግሞ ለወንጀል ድብቃ ከወያኒ ጎን የቆሙትን ሆነ ታሪክን ከልሰው ሊያወግዙን ለተነሱትም ምላሻችንም የተለወጠ አይደለም ። ያ ትውልድ ግን ሊኮራበት የሚገባና ታሪክም መቸም የማትረሳው መሆኑን ማንም ሊሰርዝ አይችልም ። ። መሪ ያልናቸውም ወኔ ቢሶችና የስልጣን ጥመኞች ሳይሆኑ ለሕዝብ የተሰው፤ አንበገርም ያሉ፤ ያልካዱ፤ ሌሎችን እንዳያጋልጡ መሰዋትን የመረጡ፤ መርዝ ከኪን የሚውጡ፤ እናቸንፋለን ብለው ሞትን የሚጋፈጡ ነበሩ ። የሰው ሰዎች፤ሀገር ወዳድና ፍርሃትን ያሸነፉ ያኮሩንና አሁንም የሚያኮሩን ብዙዎች ። እንደ እንክርዳድ ብቅ ያሉት፤ ለግል ስልጣን የባከኑት፤ ጠቋሚና ከሀዲ የሆኑትንም ድርጅቱ ባለው አቅም ታግሏል፤ አስወግዷል (አንጃዎች ያደረሱትን ከፍተኛ ጉዳት ያጤኗል!) ። የድርጅቱ ዋናው መለያው ግን በትግል መሞት ሕይወት/ ዳግም ትንሳኤ ልደት ብሎ ለዲሞክራሲ፤ለሕዝብ ሙብትና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መታገሉ ነው ። ጓዶቻቸውን ከገደለው ፋሺስትና ዘረኛ ወያኔ ተገልብጠው የሰመሩና የተቃቃፉ እንደነብሩና እንዳሉም ረስተን አንገኝም ። ኢሕአፓ ወደ ራስ መከላከልና የከተማ ተኩስ የተገፋው በገዢዎችና ጭፍሮቻቸው መሆኑን ታሪክ የመዘገበው ነው ። የታገለን ትውልድና ያታገለን ድርጅት ማውገዙ ከሰፈነና ለሀገር መሰዋት ሞኝነት ተብሎ ለሰላቅ ከተዳረገ ተኪ ጀግና፤ ትግልን አፍቃሪ አርበኛ ቢጠፋ የሚያስገርም አይሆንም ። ልቡ የሸበተን ትውልድ ወያኔም የኢትዮጵያ ጠላቶችም ይፈልጋሉ ። ትግል ደግሞ እውን ከተደረገ መራራ ነውና ፈሪ ተለይ እንጂ ፈሪና ደካማው ይምራን የሚባልበት አይደለም ።

ማንኛውም ትግል ሆነ ክስተት ብቅ ባለበትና በተካሄደበት ሁኔታ ውስጥ ነው መመርመር መገምገም ያለበት ። የጀግናው ትውልድም ትግል ዛሬ በኋላ በሚወጣለት አቃቂር የጊዜ ክልል ሳይሆን የተካሄደው ያኔ በ 66ና ሰባዎች መጀመሪያ ነው ። ርዕዮቱ፤መፈክሮቹ፤አደረጃጀቱና ህቡዕነቱ፤ ወዳጅ ጠላት አፈረጃጀቱ፤ ስምሪቱ ሁሉ የነበረበትን ሁኒታና ጊዜ አጣቅሶና ይዞ

መታየት ያለበት ነው ። ጸረ ኢምፔሪያሊስት ትግሉ ደግሞ የግድ ነበር ። የአሜሪካንን ሰው በላ ስርዓትም አልፈልግም ማለት የሚያስመሰግነው ነው ።ዛሬም ቢሆን የህብረሰቡን መሰረታዊ ሙብት ለሚያስከብር ዴምክራሲያውና ሕዝባዊ ስርዓት ይታገላል እንጂ ለሰው በላ ካፒታሊዝም መስዋዕት የሚሆን አይደለም ። ሊበራል ካፒታሊዝም ወይም የአሜሪካ ስርዓት በሚል የሚጮሁት ሆኑ ወይም አብዮታዊ ዴሞክራሲ ብለው የሚያሾፉትን አምባገነኖች አልተቀበላቸውም፤የሚቀበላቸውም አይሆንም ። የያኔው እንቅስቃሴ ግራ ክንፍነት ደግሞ የሚመለጥም አልነበር ። አሌ ብሎ ወደ ቀኝ ሊያዘም የሚፈልግ ሀይልና እንቅስቃሴ ካለመታየቱ ሌላ ለባዕድ ተገዢ ከሆነው ከአቀባባይ ከበርቴው ሌላ የጥገና ለውጥን ሊያቀነቅን የሚችልም ይህ ነው የሚባል ከበርቴ መደብ አልነበረም ። በዓለም አቀፍ ደረጃም የምዕራቡ ጎራ የቅኝ ገዢዎች፤የአፓርታይድ ደጋፊዎች፣ የጭፍን በዝባዦችና የዘረኞች ሰፈር ነበር ፡፡ ሳንቶ ዶሚንጎ፤ኩባ፤ ቪየትናም ላኦስ ካምቦዲያ፤ አንጎላ ሞዛምቢክ፤ ጊኒ ቢሳው ናሚቢያ፤ አልጄሪያ የመን፤ሌባኖን ፓለስታይን፤ኬንያ ...ስንቱ ሰቆቃ ተነስቶስ ያልቃል ? ለሕዝብ መታገል ከተባለ ከተራማጅነትና ግራ ክንፍ ከመሆን በመለስ ሌላ አማራጭ አልነበረም።

ከዚህ በተያያዘ መነሳትና ጫና ሊሰጠው የሚገባው የአደረጃጀትና የትግልም ስልት ጉዳይ ነው ። በዚህ መስክ ብዙ ተመክሮ አለ ። የዛሬ ስልጡን ፖለቲከኞች ግን ይህን ተመክሮ ከቁም ነገር ባለመቁጠራችው የተነሳ የብዙ ዜጋ ሕይወት አልፏል፤ ብዙዎች ለስየልና እስር ተዳርገዋል ። ይህ ሁኔታ ካልተቀየረ አሁንም ትግል ለአደጋ  መጋለጡ አይቀሬ ነው ። ታሪክ ይታወስ ስንል ያለፈውን ለማስታወስ ብቻ ሳይሆን የዛሬና ነገን ትግል አቅጣጫ ለማስያዝም ነው ። ኢሕአፓ ራሱ ለጥቃት የተጋለጠው በዚህ መስክ ዘረክረክና ላላ ሲል ነው ። ማዕከላዊነትና ህቡዓዊነት--ትግሉ የግድ የሚላቸው መርሆች-- በተገቢው መንገድ በስራ ላይ መዋል ሲያቅታቸው ክፉ እየተፈታ ጉዳት ይከተላል ። ጠበቅና ሙያተኛ የሆነ ደርጅት/አደረጃጀት መኖሩ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ በጥቂት የአመራር አባሎች ዲሞክራሲያው ግንባር (ዲኤፍ) በሚል አባልና ደጋፊን የሚያደባልቅ አወቃቀር መምጣቱ፤ ህቡዕነት መዳከሙ፤ ሁሉም አካላት/ተቋማት የየራሳቸው ስኳድ ማቆማቸውና፤ ማወቅ ካለበት በላይ ማወቅ አይገባም የተባለው ዋና መርህ በመሻሩ አንድ ሲያዝ ወይ ሲከዳ ብዙ ጓዶችና መዋቅሮች የሚመቱበት ሁኔታ ተፈጠረ ። ይህ አንዱ ገጽታ ሲሆን በሌላ ደረጃ ደግሞ ካለው አገዛዝ ጋር የሚያብሩ ለሹመትም ሆነ ሌላ የአባላቸውን ስም ለጊዜያው ወዳጃቸው እየሰጡ ለመጪው እርድ ራሳቸውን ያመቻቻሉ። ያየነው ነው በደርግም በወያኔም ጊዜ። ዓለም ሰለጠነ፤ፖለቲካም ክፍት ሆነ፤ በሰላምና በግልጽ መታገል ነው እንጂ የምን ህቡዕነት በሚባልበት በዘመናችን፤ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ  የየሀገሩን ተጨባጭ ሁኔታ መርምሮ ተገቢውን ስልትና አደረጃጀት አሰራር መቀየስ ሲገባ ይህ ተብሏልና ማለትም ሰላምን ግልጽነት ተሰብኳልና በረቱን ክፍት አድርገን ለሁሉም ተኩላና ቀበሮ እንተውለት ማለት ጉዳት እያደረሰ ነው ። ህጋዊነትን አገኘን፤ የምንታገለው በሰላም ነው ቢባልም ሀይልን ሁሉ አለማጋለጥ የፖለቲካ ሀ ሁ መሆን ነበረበት ። ይህ ግን አልሆነም ። የድርጅቶች ገበና በየአደባባዩ ይሰጣል፤ምስጢራቸው ይዝረከረካል፤ በድርጅቶች ላይ ከፋፋይና የወያኔ ተገዢ ሆነው የሚነሱት ክፍሎች ምን ያህል ወያኔን እንደጠቀሙት የምናውቀው ነው ። የምዕራቡ የፖለቲካ ሁኔታ በኢትዮጵያ የሚሰፍን መስሏችው፤ወያኔንም ካለውና ከማይለቀው አውሬነት ነጥለው ሊያዩ የቃጡ ከወያኔ የሚገባቸውን ቅጣት ሲቀበሉ የሕዝብን ትግልንም በዚያው ጎድተዋል ። የኢሕአፓ የቀድሞውና የዛሬው ህቡዕነት ለየቅል ቢሆንም የድርጅትን አወቃቀር በምስጢር መያዝ ፤ ሁሉንም አመራርና አባላት አለማጋለጥ (ለምሳሌ በኢትዮጵያ ያሉ ቀርቶ በውጭም ያሉ የ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ሁሉም በአባሎች አለመታወቅ ድርጅቱን ከጥቃት ጠብቆት መቆየቱ የሚታወቅ ነው) ። በግልጽነት እንታገል ብለው አቅዋም የያዙም የዚህን ገደብ ማወቅና መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል ። በዲሞክራሲ ስር ሊኖር የሚችል ሰፊ ሕዝባዊ ፓርቲ ይዘትና አደረጃጀት አምባገነኖች በስልጣን ባሉበት አደገኛ ሁኔታ ሊኖር ሊገኝ ሊታሰብና ሊያዝም የሚችል አለመሆኑን የኢሕአፓ ተመክሮ ያስረዳል ።

እንጻፍ ካልንማ በሚል አቢይ ጉዳዮችን በተመለከተ መጻፉ ግድ ሆኖ የመጣው ያ በሁሉም አባላት ተሳትፎና የጋራ ጥረት የሚጻፈው ታሪክ ለህትመት እስኪበቃ የዋሾዎች ወሮበላ ቡድንና ወያኔ የወጣቱ አንጎል ላይ የእንዶድም የኦሞም አጠባ እንዳያካሂዱ ለማድረግ ነው ። በታሪክ ስም ሀቀኛ ታሪክን ሊያጠፉና እግረ መንገዳቸውንም ወደዱም ጠሉም ወያኔን ሊጠቅሙ የተነሱትን ከነውሸታቸው ማጋለጥና መከላከል የግድ በመሆኑ ነው ። ይህን ስናደርግ ያው ቀደሞም እንደተባለውም ዶሴን ከፍቶ የመዘርገፉ ጊዜ ገና ነውና አሁንም ቢሆን መቆጠብ የግድ ሆኗል ። ድርጅቱ ዛሬም በትግል ላይ ያለ ነውና ፤በሚናገረውና በሚያወጣው ምስጢርም አሁንም ሊጎዳ የሚችልበት ሁኔታ አለና እንደ ግለ ሰቦች ሀላፊነት የጎደለውን የጽሁፍ መፉለል ሊያስተናግድ አይችልም ። የአንዳንዶቹን ገበና--ያውም አላርፍ ያለች ጣት ሲሆኑ ሳይቀር--አፍኖ የሚይዘውም ለዚህ ነው ። ሌሎችንም በተመለከተ ይህ ተደርጎ፤ተወስኖ ነበር ማለቱ ጊዜው ገና ሆኖ ያስቸግራል ። ባለውና በሚታወቀው ቢሆንም ኢሕአፓ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ የታገለና የደም ዋጋ የከፈለ፤አሁንም ቢሆን ለማንም ባዕድ ሳይሰግድ፤ሀገርና ሕዝብን ሳይከዳ እየታገለ መቀጠሉን ማንም ጮሌ ሆነ መደዴ ዋሾ ሊሰርዘው የሚችል አይደለም ። አሁንም ቢሆን ከወያኔ ጋር እንተቃቀፍ፤ ሰላም በሚል ሰበብ ወያኔን አምርረን መታገሉን እንተው፤ ሁለገብ ትግል ማለት ጊዜው አልፎበታል ከሚሉት ጋር  ኢሕአፓ የሚግባባ አይደለም ። ውሻ ወደ ትፋቱን ድርጅቱ አያውቅም ። ጊዜው ያለፈበት ትግል ሳይሆን ጭቆናን ተሸክሞ መኖር ነው ። ወያኔና መሰሎቹ እንደሆነ የሌባ ዓይነደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ ናቸው ። የወያኔ ውድቀት ደግሞ በምርጫ ድምጽ ሳይሆን በአመጽና ጥይት መሆኑን ለካዱት አሁን የተጠናቀቀው የምርጫ ጨዋታም ውጤት አሳይቷቸዋል ። የአመጽን ዋናነት በኢትዮጵያ ኢሕአፓ የተረዳው ከ43 ዓመት በፊት ነው ። ይህ ነው ታሪክ--እንጻፍ እንናገር እንዘክር ከተባለ ። የሰማዕትን ደምና መስዋዕትነትም የምናከብረው ከገድላቸው ትሁት ሆነን በመማር ነው።

ይቀጥላል.........